## አንተም ጌታን ጥራው

ጌታን መድህናችንን በጅራፍ ገረፉት
የእሾክ አክሊልም በራሱ ደፉበት
መስቀል አሸክመው እንዲሰቀልበት
አያዳፉ ጌታን ጎልጎታ ወሰዱት።
 አቤት ያስገርማል የጌታችን ፍቅር
 እንደ በደለኛ ከወንበዴዎች ጋር
 ፈቀደ ሊሰቀል ሳይለው እንኳ ቅር።
አንደኛው ወንበዴ አፉን ከፈተና
የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እስኪ ውረድና
ከሳሽህን ተበቀል እኛንም አድና!
እያለ አሾፈበት አዳኙን ናቀና
የሞት አፋፉ ላይ መሆኑን ረሳና።
 ሌላ ባልንጀራው ያለ ባጠገቡ
 የተናገረውን አዳምጦ ከልቡ
ተይዘህ ስትሄድ በሞት ክፉ ጉልበት
ይቅርታን ብታገኝ ንስሀ እንደመግባት!
አትፈራም አምላክን ይህን ስትናገር?
ጻድቁን መድኃኒት እንዲህ ስትዳፈር።
 የኔና ያንተ ፍርድ ያሁኑ መከራ
 ተገቢያችን ነው እኮ ለፈጸምነው ስራ
 ስንዘርፍ ስንገድል ወንጀል ስንሰራ
 ኖረን ስለሆነ አምላክን ሳንፈራ።
ኃጢያት የለበትም ይኸ ሰው ንጹህ ነው
መከራ የሚቀበል ስለኛ ኃጢያት ነው
አለና ዞር ብሎ ጌታን እየጠራው
እባክህ አስበኝ ብሎ ተማጸነው ።
 ዕውነት እልሀለሁ ዛሬውን በገነት
 ይዤህ እገባለሁ በጸጋዬ ብዛት
 ብሎ ቃል ገባለት ከፍርድ ሊያድነው
 ያለፈ በደሉን በደሙ አነጻው
 ቆጥሮለት እምነቱን ከገነት አስገባው።
ይህንን ወንበዴ ጌታ ይቅር ካለ
በንስሐ ጸሎት ኃጢያቱን ካስጣለ
አንተንም ይወዳል የፍቅር ልብ አለው
አድነኝ በልና ብቻ አንተ ጥራው።

ለሚጠሩት ሁሉ ባለጠጋ ነውና
የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ
ይድናልና።
ሮሜ 10፡13

